# ታዛቢዋ እመቤት

አገሬ ከሰዊድን

20100604

ላልሰሙት አሰሙ ፤ ዛሬም መርዶ መጣ
ለግፉ ጭፍጨፋ ፤ እርም እንድናወጣ ።
ታዛቢዋ እመቤት ፤ አማረች ገላኔ
በታዘበች ሞተች ፤ ኡ ኡ በል ወገኔ
የሰቆቃው ኑሮ ፤ ነውና ነግ በእኔ ።

አይኗ ባየ ጠፋች ፤ አለፈ ህይወቷ
ልጆቿም ተቆሉ ፤ በጥይት ከፊቷ
ባስተዋለች ቅጣት ፣ ተበተነ ቤቷ ።

በደም የጨቀየው ፤ የወያኔ ዙፋን
በቤተሰቡ ፣ ደም ተረጋግቶ ይሆን?
ለመላው ኢትዮጵያ ፤ አንድነት ታዝባ
በደም እየዋኙ ፤ ሳትጠርግ የልጅ እንባ
በቀማኛው ገዥ ፤ ሆናለች ሰለባ ።

መችም ያለአባት ነው ፤ የዘንድሮዉ ፍርድ
ምን እያሾመ ነዉ ፤ ምንስ ቢያሶድድ
በየቤቱ ገብቶ ፤ ሴትን ማሳደድ?
አሸነፍኩኝ ያለው ፤ አገር ወደደኝ
አሁን ምን መጣበት ፤ በደም የሚያሷኝ?

የሂ የግፍ ጽዋ ፤ ታምቆ ታምቆ
የገነፈለ ቀን ፤ ትግስቱ ሁሉ አልቆ
አሸነፍኩኝ ያለው ፤ ኮሮጆዉን ሰርቆ
የት እንደሚገባ ፤ መውደቂያውን አውቆ
ከቶ አስቦት ይሆን ፣ የሄንን አርቆ?

EthioLion.Com

EthioLion.Com